# ድንግል ማርያም

ድንግል ማርያም የእኛ አማላጅ (፪)
ከአብርሃም ዘር የተመረጠች
በንፅህና ጌታን ወለደች (፪)

መሶበ ወርቅ የመልካም ሙዳይ
ቤተልሔም ሆይ እሙ ለፀሀይ
የካህናቱ የወርቅ ማዕጠንት
የዛን መዓዛ ነሽ ደግ ፍጥረት

አዝ...

የመለኮት አትሮንስ የኮሬብ ተራራ
የወርቅ መቅረዝ የአሚናዳብ ሠረገላ
ቤትሽ ሰርግ ቤት የብርሃን ድንኳን
የአምላክ ማደርያ ታቦተ ጽዮን

አዝ...

የአቤል የዋህት የሴት ቸርነት
የዮሴፍ አፅናኝ ርህት የዋሂት
የአሮን ፀናፅል የጌዲዮን ጠምር
የሰለሞን ጥበብ የዳዊት መዝሙር

አዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org